

‹‹አራት ዓመት በሃኪም ቤት፣ 9 ዓመት በአልማ የቤተሰብ ምጣኔ አግልግሎት ተጠቃሚ ነን። እኔ በግለሰብ ቤት ውስጥ በ60 ብር ተቀጥሬ ነበር የምሰራው። ያኔ ትልቋ ልጅ ተወለደች። እሷን ለማሳደግ ተቸግረናል። ለክርስትናዋ እንኳን መደገሻ አጥተናል። በዚህ ምክንያት ሁለተኛ መድገምንም እንኳን አልመኘንም ነበር። ነገር ግን ተወለደች። በሃኪም ቤት እገዛ ሦስተኛ እንዳይወለድ አድርገን ቆየን።

‹‹እስከ ዛሬ ድረስም ገቢያችን ትልቅ ነው የሚባል አይደለም። ልጅ አለማብዛታችን ግን እንድንቆጥብ አድርጎናል። አሁንም በ100 ብር ደሞዝ የገበሬዎች አግልግሎት ጽ/ቤት የጥበቃ ሠራተኛ ሆኜ ነው የምኖረው። በመቆጠባችን ግን በጎች ገዛን። አንዲት ላምም አለችን። ወርልድ ቪዥንም ሌላ ላም ሰጠን።

‹‹ልጆቻችን አይራቡብንም። አይራቆቱብንም። በምግባቸውም ሆነ በልብሳቸው አቅማችን በሚፈቅደው መጠን እንንከባከባቸዋለን። ሁለት ስለሆኑና በደንብ ስለምንይዛቸው በአመጋገብ ጉድለት ወይም በኑሮ ጉስቁልና የሚመጣ ህመም የለባቸውም። ጤነኞች ናቸው። የአዕምሮ ጭንቀት የለባቸውም። ሰውነታቸውም የተጎዳና የከሳ አይደለም።

‹‹ልጆቻችንን እያስተማርናቸውም ነው። ትልቋ ብዙዬ ትባላለች። የ7ኛ ክፍል ተማሪ ነች። ትንሿ ሰላም ደግሞ 6ኛ ክፍል ደርሳለች። ትምህርታቸውን አቋርጠው አያውቁም። የትምህርት መሳሪያ አይቸግራቸውም፤ እኛው ነን አሟልተን የምንገዛላቸው።

አቶ መኮንን ታዬ

# ወይዘሮ ቀለሚ አበበ

## ከሰሜን ሸዋ ዞን፣ አንጎለላና ጠራ ወረዳ፣ ኮቱ ቀበሌ



‹‹የአሁኑ ባለቤቴ መውለድ ይፈልጋል፡፡
‘እነዚህን ለቁምነገር ሳብቃ›
ብዬ ስነግረው ያደምጠኛል፡፡



‹‹ሁለት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ልጆች አሉኝ፡፡ አምስቱም ይማራሉ፡፡ ሁለቱ ዘንድሮ (2001 ዓ.ም) የ10ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ጨርሰዋል፡፡ አንዱ 7ኛ፣ አንዷ 5ኛ ናቸው፡፡ ትንሹ የ2ኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ ሁሉም ትምህርታቸውን አቋርጠው አያውቁም፡፡

‹‹ድሮ የ8ኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ ጠልፎ የወሰደኝ ባል ነበረኝ፡፡ እነዚህን አምስቱንም ልጆች ከእሱ ነው የወለድኳቸው፡፡ አከታትዬ ስለወለድኳቸው ሰውነቴ እየኮሰሰ ይሄድና እደክም ነበር፡፡ ባለቤቴ ግን ከዚህም በላይ ብጨምርና አስርም ብወልድ ስለሚፈልግ ጣጣ አልነበረውም፡፡ ሴት ልጅ መቀጫዋ አከታትሎና አብዝቶ መውለድ ነው፡፡ የምጐዳው እኔ ነኝ፡፡ እሱ ምኑ ተነካ!? በዚያ ላይ ጠጪና ሰካራም ስለነበረ በፍርድ ቤት ተፋታንና ሌላ አገባሁ፡፡

‹‹የአሁኑ ባለቤቴ መውለድ ይፈልጋል፡፡ ‘እነዚህን ለቁምነገር ላብቃ› ብዬ ስነግረው ያደምጠኛል፡፡

‹‹የተዋልዶ ጤና አግልግሎት ተጠቃሚ መሆን የጀመርኩት አልማ ከመጣልን ጀምሮ ነው፡፡ ዘጠኝ ዓመት ሆነኝ፡፡ ከራሴ ተርፎ ሌሎችንም እየመከርኩኝ ተጠቃሚ ሆነው ወደ ምርት እየተሰማሩ ነው፡፡

‹‹አሁን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን! ጤነኛ ነኝ፡፡ ወደ ሥራም እሰማራለሁ፡፡ የግብርና ሥራና ከብት ማርባት እሰራለሁ፡፡ እነግዳለሁም፡፡ ጥማድ በሬ አለኝ፡፡ የእርሻ መሬት አለኝ፡፡ ላሞችና በጎችም አሉኝ፡፡ ከአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም (አብቁተ) እየተበደርኩኝ እየሠራሁ የራሴን ቤት ሠርቻለሁ፡፡



‹‹የአልማ ወኪሎች የሚያስተምሩን ብዙ ነው፡፡ አንድ ለአንድ ስለመወሰን፣ ከጋብቻ በፊት የደም ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ ያስተምሩናል፡፡ የሚነግሩንን ተግባራዊ እያደረግን ነው፡፡

‹‹ይህ የአልማ ጉዳይና የእኛ በትልቁ መጠቀም በመፅሔት ቢወጣ ጥሩ ነው፡፡ ለልጆቻችንም መማሪያ ይሆናል፡፡ ይህ የአልማ ትምህርት ቀደም ብሎ ቢኖር ኖሮ መልካም ነበር፡፡ አልማን ከማንም በላይ የማመሰግነው ድርጅት ነው፡፡ የበለጠ ያስፋው፣ ያስፋፋው፡፡››

# በደቡብ ወሎ ዞን ተንታ ወረዳ የአልማ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት

*መላከ ፀሐይ ወርቅነህ አሰፋ በተንታ ወረዳ 06 ቀበሌ ነዋሪ ናቸው። በአካባቢያቸው በተዋልዶ ጤና አገልግሎት በተለይም ጉጅ ልማዳዊ ድርጊቶችንና የኤች አይቪ ኤድስ ቫይረስ ስርጭትን በመከላከል እንዲሁም በቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ዙሪያ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ወክለው ያገለግላሉ። 16 የጤና ፓኬጆችን በመተግበር በተንታ ወረዳ በሞዴልነት ከተመረጡት አርሦ አደሮች መካከልም አንዱ ናቸው።*



*መላከ ፀሐይ ወርቅነህ አሰፋ*

"ያለዕድሜ ጋብቻ፤ የሴት ልጅ ግርዛት፣ ግግ ማውጣትና መሰል ጉጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከል አስተምራለሁ። ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን በመከላከልና የተመጠነ ቤተሰብ እንዲኖር በማድረግ በኩልም ከአልማ ወኪሎች ጋር በመነጋገር እንዲሁ እሰራለሁ።

ሠርግ፣ ተስካር እየተባለ በሚደረግ ድግስ የኮርቻ በቅሎ፣ የወተት ላም፣ የቀንበር በሬ እንዳይሸጥ ቤተክርስቲያንን ወክየ አስተምራለሁ። በተዋልዶ ጤና ረገድም አራርቆና መጥኖ ባለመውለድ እናቶች በጤናቸው ላይ ጉዳት የሚደርስባቸው ከመሆኑም ባሻገር የሚወለዱት ህፃናት በተገቢው እንክብካቤ አለማደጋቸው ሌላው ችግር ነው። አምስት ደካማ ልጆች አከታትሎ ከመውለድ በማራራቅ ቦቸስ ቦቸስ ያሉ ቶሎ አድገው ቶሎ የሚላኩ፤ ቶሎ ለስነ-ምግባር የሚደርሱ ልጆችን መጥኖ መውለዱ ፋይዳው የጉላ ነው። በሌላ በኩል አንዱን ስታጠባ ሌላውን ሣታሣድግ እንደገና በማርገዝ በወላጅና በልጆች ላይ ከሚደርሰው ጉስቁልና ባሻገር እናቶች በዚህ ሁኔታ በቤት ውስጥም ሆነ በውጭ ባለቤታቸውን ማገዝ አለመቻላቸው እንዲሁ ሌላው ችግር ነው።"